# ልጅዎ አለበት ብለው ያስባሉ

# የኩፍኝ በሽታ?

## ልጅዎ የኩፍኝ በሽታ አለበት ብለው ካሰቡ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

**ኩፍኝ ብዙውን ጊዜ ትኩሳት፣ ሳል፣ የአፍንጫ ፍሳሽ እና የአይን መቅላት ይጀምራል፤ ይህም ወደ ሽፍታ ይመራል። በቤተሰብዎ ውስጥ ያለ አንድ ሰው የኩፍኝ በሽታ ምልክቶች ካለባቸው፦**

**ከልታመሙ የቤተሰብ አባላት** ያርቋቸው።

**ጎረቤቶችዎን ወይም ከቤትዎ ውጭ ያሉ ሰዎችን እንዳያሳምሙ** በቤት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው ቤት ውስጥ መቆየት አለበት።

**በቤትዎ ውስጥ ያለ አንድ ሰው በኩፍኝ በሽታ እንደታመሙ ለማሳወቅ** ለዶክተር ወይም ሆስፒታል ወዲያውኑ ይደውሉ። መመሪያዎችን ይሰጡዎታል።



## ወደ ድንገተኛ ክፍል መቼ መሄድ እንዳለበት

**የታመመው ሰው በፍጥነት በጠና እየታመሙ ከሄዱ ወይም ከታች የተዘረዘሩት ምልክቶች ካሉባቸው ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ይውሰዷቸው።**

**አይጠብቁ።**



**የመተንፈስ ችግር**
(ወይም ከወትሮው በበለጠ ፍጥነት መተንፈስ)



**በሚተነፍሱበት ወይም በሚያስሉበት ጊዜ ህመም**



**ድርቀት**
(ደረቅ አፍንጫ እና አፍ፣ ሽንት መቀነስ፣ እንባ ሳያወጣ ማልቀስ)



**የማይቆም ትኩሳት ወይም ራስ ምታት**



**ግራ መጋባት፣ የንቃት መቀነስ ወይም ከባድ ድክመት**



**በአፍ ዙሪያ ሰማያዊ ቀለም፣ ዝቅተኛ ኃይል ወይም ለመመገብ መቸገር**
(ለታዳጊ ልጆች)

**ከመድረስዎ በፊት አንድ ሰው እንዲደውል ያድርጉ። በኩፍኝ የታመመ ሰው እየመጣ መሆኑን ለሆስፒታሉ ያሳውቁ።**

ለኩፍኝ ዝግጁ ይሁኑ
cdc.gov/measle
CDC